የሰበር መ.ቁ. 15631

ታህሣስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ሐጐስ ወልዱ
3. አቶ ዳኜ መላኩ
4. አቶ አሰግድ ጋሻው
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካቾች፡-** 1ኛ. የሻረግ መንግሥቱ
2ኛ. ሰገዶ መንግሥቱ

**ተጠሪ፡-** እማሆይ የሻረግ ፈረደ

***ስለ ይርጋ - የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነው ጊዜ - የይርጋ ጥያቄ በፍርድ ቤት ተቀባይነት የማይኖርበት ሁኔታ - የፍ/ብ/ህ/ቁ 10001/2/፣ 1168፣ 1845፣ 1853***

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ተጠሪዋ የሚች አባታችን የአቶ መንግሥቱ ዘወልዴን ቤት ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክስ መርምሮ የሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የጎንደር ወረዳ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ያፀናውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ።

**ዉሳኔ**፡- በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል።

1. ውሎች ንብረትን በተመለተ በ1675 መሠረት የሚደረግ ስምምነት በመሆኑ በዚሁ መሠረት ትርጉም የሚሰጠው የውል ሰነድ ሳይኖር በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845ን በተመለከተ የሚሰጥ ውሳኔ የለም።
2. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለዕጅ /ባለይዞታ/ የሆነ ሰው የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት ከከፈለ ሌላ ይገባኛል የሚል ሰው እንዲሰጠው ሊጠይቀው አይችልም።



የሰበር መ.ቁ. 15631

ታህሣስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** 1. መንበረፀሐይ ታደሰ
2. ሐጐስ ወልዱ
3. ዳኜ መላኩ
4. አሰግድ ጋሻው
5. ሂሩት መለሰ

**አመልካቾች፡-** 1ኛ. የሻረግ መንግሥቱ
2ኛ. ሰገዶ መንግሥቱ

**ተጠሪ፡-** እማሆይ የሻረግ ፈረደ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 364 በይግባኝ ደረጃ ቀርቦለት በነበረው ጉዳይ ሲያከራክር ቆይቶ የካቲት 16 ቀን 1996 ዓ/ም መረምሮ የሰሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የአሁኑ አመልካቾች ተጠሪዋ የሚች አባታችን የአቶ መንግሥቱ ዘወልዴን ቤት ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የሰጠው ውሣኔ ነው። የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔው ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጐንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /1/2/ እና 1845 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የወሰነው በሕጉ አግባብ ነው በማለት አጽንቶታል።

አመልካቾች አባታችን አቶ መንግሥቱ ዘወልዴ ከሞቱ በኋላ በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባውን ቤት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት ተረክበን ተጠሪዋ ባይወልዱንም እናታችን ናቸው ብለን በማሰብ እንዲቀመጡበት ያደረግነውንና በአክብሮት ሣንጠይቃቸው የቆይነውን ንብረት እንዲያስረክቡን በማለት ያቀረብነው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል

በሚል ለሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ንብረቱን ሣንጠይቅ የቆየነው በቤተዘመድ ግንኙነት ምክንያት ተጠሪዋን በመፍራትና በማክበር ስለሆነ ፍ/ቤቱ የይርጋውን ክርክር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853/1/ መሠረት ሊቀበለው አይገባም ባዮች ናቸው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በአመልካቾች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለአሁኗ ተጠሪ እንዲደርሳቸው ተደርጎ ሐምሌ 18 ቀን 1996 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የመልስ መልስ ሰጥተውበት ተከራክረዋል፡፡

በተጠሪዋ በኩል የቀረበው ክርክር ሲታይ አመለካቾች እኔን የእንጀራ እናታቸውን በማክበርም ሆነ በመፍራት መብታቸውን ሣይጠይቁ ቆይተዋል ሊባል ስለማይችል ፍ/ቤት ይርጋ አልቀበልም የሚልበት ምክንያት የለም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ችሎቱም የአሁኑ አመልካቾች ከ1962 ዓ/ም በፊት የሞቱትን የአባታችንን ቤት ይዘው የሚገኙት የአሁኗ ተጠሪ ሊያስረክቡን ይገባል በሚል ያቀረቡት ክሥ በይርጋ ቀሪ ሆኗል አልሆነም፣ ፍ/ቤት ይርጋ አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለውን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጐንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ከአባታችን በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባውን ቤት የአሁኗ ተጠሪ ምንም አይነት መብት ሣይኖራቸው ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆን ይዘው ስለሚገኙ ሊያስረክቡን ይገባል በሚል ያቀረቡትን ክስ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በአሥር አመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሊወሰኑ የቻሉት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም ተደርጓል የተባለውን ውል መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ከሰነዱ እንደሚታየው ግን ቤቱን የአሁኗ ተጠሪ ለቀው ለሟቹ ለአቶ መንግሥቱ ዘውልዴ ወራሾች ማሥረከባቸው እና ሌሎችን ንብረቶችም ስለመከፋፈላቸው



ከመገለጹ በቀር የሟቹ የአባታቸው ሚስት በቤቱ እየተጠቀሙበት ይቆዩ ወይም ይኑሩበት የሚል ነገር የለውም፡፡ ከዚህ ሌላ ቤቱ በሟች ሚስት ይዞታ ሥር ቆይቶ ወደፊት በዚህ ጊዜ ለወራሾች ያስረክባሉ የሚል የውል ቃል የለውም፡፡ በሰነዱ ላይ የሰፈረው በሕግ የውል ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ ውል ማለት ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1675 ላይ እንደተመለከተው ንብረታቸውን የሚመለከቱ ግዴታቸውን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ሥምምነት ስለሆነ በዚሁ መሠረት የውል ትርጉም የሚሰጠው ነገር ሣይኖር ውል አለ የሚል መነሻ በመያዝ ይርጋን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ስለውሎች በጠቅላላው በሚለው የፍትሐብሔር ሕጉ ክፍል ተጽፎ የሚገኘው በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 ላይ የተመለከተው የአሥር አመት ጊዜ ነው ብሎ መወሰን ትክክል አይደለም፡፡ በአሁኑ አመልካቾች በኩል የቀረበው የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም የተፃፈው ሰነድ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ጋራ በተያያዘ የሚያስነሣው የይርጋ ጥያቄ ስለሌለ በዚህ ጉዳይ የተጠቀሰው የይርጋ ሕግ አግባብነት የለውም፡፡

በሌላም በኩል የአሁኗ ተጠሪ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሲከራከሩ የነበሩት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም ተፃፈ የተባለውን ሰነድ መነሸ በማድረግ ብቻ ሣይሆን ቤቱ ከ1943 ዓ/ም ጀምሮ ባለማቋረጥ ግብር እየከፈልኩበት ንብረቴ ሆኗል፣ ከሃያ ሰባት አመት በላይ በስሜ ስገብርበት ቆይቼ የቤቱ የቦታ ይዞታም ሆነ የቤቱ ባለቤትነት ሥም በሥሜ ሊሆን ችሏል በሚል ምክንያት ጭምር ሲሆን እነዚህ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሆናቸውን ከመዝገቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ፍሬ ነገሮች በመነሣት በሕጉ በኩል ያለው ሲታይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ /ባለይዞታ/ የሆነ ሰው የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት በሥሙ ከከፈለ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል በሚል ደንግጐ ይገኛል፡፡ ሕጉ

ይርጋ አዘል ስለሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ /ባለይዞታ/ የሆነው ሰው የዚህን ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ለ15 ዓመት በሥሙ ከከፈለ ሌላ ይገባኛል የሚል ሰው እንዲሰጠው ሊጠይቀው አይችልም፡፡ በሕጉ ለባለይዞታው መብቱ ይረጋለታል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ባለይዞታ በመሆን የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ከ15 ዓመት በላይ በሥማቸው ሲከፍሉ ስለቆዩ በሕጉ የዚሁ ሀብት ባለቤት ሆነዋል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች አባት ከ1962 ዓ/ም በፊት የሞቱ ስለሆነ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተጠሪዋ ይዞታ ሥር የቆየውን ቤት ከሃያ ስምንት አመት በኂላ እንዲያስረክቧቸው ያቀረቡት ክሥ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

አመልካቾች ክስ ሣናቀርብ የቆየነው ተጠሪዋ የሚቹ አባታችን ሚስት በመሆናቸው በመፍራትና በማክበር በመሆኑ ፍ/ቤት ይርጋውን ሊቀበለው አይገባም በሚል ያነሱትን ክርክር በተመለከተም በእርግጥ ፍ/ቤት ይርጋን አልቀበልም የሚልባቸው ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 የተዘረዘሩት ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ባለገንዘቡ የሚፈልገውን ያልጠየቀበት ምክንያት ባለዕዳውን የመፍራትና የማክበር ስሜት መኖር አንዱ ነው፡፡ አመልከቾች ከሃያ ስምንት አመት በላይ ተጠሪዋ ቤቱን እንዲያስረክቡን ሣንጠይቅ የቆየነው የአማታችን ሚስት ስለሆኑ እንደ እናት ስለምናያቸው የመፍራትና የማክበር ስሜት አድሮብን ነው ይበሉ እንጅ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመለካቾች አባታቸው ከሞቱ በኂላ የአባታችንን ንብረት አካፍይን ወይም አስረክቢን የሚል ጥያቄ አንስተው ሽማግሌዎች ሰብስበው የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተፃፈ ሰነድ በተደረገ እርቅ ንብረት መከፋፈላቸው መገለጹና በዚሁ ሰነድ አማካኝነት ቤቱን ተረክበን ነበር ማለታቸው ሲታይ ከዚህ በኂላ ሣይጠይቁ የቆዩት ተጠሪዋን በመፍራትና በማክበር ምክንያት ነው ለማለት አይቻልም በሚል ሣይቀበላቸው ቀርቷል፡፡ በአመልካቾች በኩል ተጠሪዋን የመፍራትና የማክበር ስሜት ነበረ አልነበረም ለሚለው ፍ/ቤት መፍራትም ሆነ ማክበር አልነበረም የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ ወደ ፍሬ ነገር ጥያቄ ስለሚያመዝን በሰበር ደረጃ ሊመረመር አይችልም፡፡ በሰበር ደረጃ ሊታይ የሚችለው የሥር ፍ/ቤት የመፍራትና የማክበር ስሜት መኖሩን አረጋግጦ ይርጋን አልቀበልም ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያት



አይደለም በሚል ወስኖ ቢገኝ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ሕግ ቀሪ መሆኑ ቢረጋገጥም ፍ/ቤት ይርጋውን አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት አለ በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተፃፈው ሰነድ በአመልካቾችና በአሁኗ ተጠሪ መካከል ቤቱን በሚመለከት የተደረገ የውል ስምምነት እንዳለ አድርጐ በመመልከት ይህንኑ መነሻ በመድረግ ለተነሣው የይርጋ ጥያቄ የሚመለከተው የይርጋ ሕግ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የአሥር አመት ጊዜ ነው ማለቱ የተሣሣተ ሆኖ ቢታይም ክሱ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 አንፃር ሲመረመር በይርጋ ቀሪ ከመሆን የሚድን ሆኖ ስላልተገኘ በውጤቱ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ መወሰኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ነዉ፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአሁኑ አመልካቾች በኩል የቀረበው ክሥ በይርጋ ቀሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡